የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian Peoples Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)


# አማራጮችን አፍኖ ምርጫ ለሚለው ቧልት ወጣቱ መጠቀሚያ አይሆንም!

ሰኔ 2007 ዓ.ም

## መግለጫ (ከኢወክንድ )

በፀረ-ዲሞክራሲያዊነቱና በአፋኝነቱ በዓለም ላይ ሳይቀር ሥም ያተረፈው ወያኔ ምርጫን የሚመለከተው የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት የሚረጋገጥበት ሒደት ሳይሆን በሥልጣን ላይ ለመቆየት መኖር የሚገባው ማሳሰቢያ እንደሆነ አድርጎ ነው። ድርጅታዊ ነፃነት ያላቸው አማራጭ ሃይሎችን፣ ነፃ መድረኮችና የብዙሃን ድርጅቶች በታፈኑበት አገር የጎጠኞቹ ጥርቅም በየአዓምስት ዓመቱ በሕዝብና በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ ምርጫ እያለ ሲቀልድ ሌላው ቀርቶ አያስቅም ያሉትን ሳይቀር ማሳደዱን ተያይዞታል።

ምርጫ ለወያኔ ህዝብ የተለያዩ የፖለቲካ ደርጅቶች የሚያቀረቡለተን የፓለቲካ አማራጭ አይቶ ለህልውናውና ለጥቅሙ የሚበጀውን መርጦ ለመንግሥት ሥልጣን የሚያበቃበት ሂደት ሳይሆን ራሱ ወያኔ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ ራሱ በሥልጣን የሚቆይበትን ሁኔታ የሚፈጥርበት ሂደት ነው። በወያኔ አገዛዝ የተደረጉና የሚደረጉ ምርጫዎች ሁሉ የይስሙላ የሆኑትና የሚሆኑትም አምባገነናዊ አገዛዙን ህጋዊ ለማስመሰል ስለሚጠቀመባቸው ነው።

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሉዓላዊ ሥልጣንና ወሳኝነት መብት ረግጦ የራሱን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አስፍኖ ዝንት ዓለሙን ከህዝብና ከህዝብ ወገኖች ጋር ጠላት ሆኖ እንደቀጠለ ነው። የሕዝቡን ሥልጣንና መብት በመግፈፍ “ሀ” ብሎ አገዛዙን በመጀመሩም ሌሎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለመጨፍለቅ ወደኋላ አላለም። ወያኔ የህዝቡን ሥለጣን ነጥቆ የራሱን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በሕዝብ ላይ በመጫኑ የኢትዮጵያ ወጣቶችና የሕዝብ ወገኖች የሕዝብን ሥልጣን ለማስመለስና ከዚህ ጋር ተነጥለው የማይታዩ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር መታገልና መሰዋእትነትም መክፈል ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ሕዝቡና ለህዝቡ የቆሙ የአንድነትና ዲሞክራሲያዊ ሀያሎች በታገሉት ቁጥር ከሕዝብ የቀማውን ሥልጣን በእጁ ለማቆየት ሲል ይበልጥ አፋኝ ፤ ይበልጥ ፅረ-ዲሞክራሲ እየሆነ የመጣው ወያኔ፣ ወደፊትም በዚሁ አፍራሽ ተልዕኮው ለመቀጠል በይስሙላ ምርጫ ዘረኛ አገዛዝ እድሜውን ለማራዘም እየተቅበጠበጠ ይገኛል ።

በአገራችን የወቅቱ ሁኔታ ሕዝቡ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ መብቱን ለማስከበር ነቅቶ የተነሳበት ወቅት ነው ማለት ይቻላል። ይህ አገዛዝ ምርጫ እያለ በሚጠራው ራሱን መልሶ የመሾም ተራ ሸንገላ ተሰማርቶ የተለየ አማራጭ ያቀረበ፣ተቃውሞ ያሰማ፣ በነፃ ለመደራጀት የሞከረ የሚያሳድድ፣ የሚያፍንና የሚገድል ለመሆኑ ከቋራ እስክ ሞያሌ፣ ከአረካ እስከ ባህርዳር፣ ከጋምቤላ እስከ አሰቦት ገዳም፣ ከበደኖ እስከ ወልቃይት፣ ከደሴ እሰከ አንቦ፣ ከወተር እስከ አፋር፣ ከባሌ አስከ አዲስ አበባ ወዘተ... የተረሸኑት ንጹሀን ዜጎች ደም ምስክር ነው።

ዛሬ በአገራችን የሚታየው ሀቅ የሚያሳየው የሕዝብ መብት መረገጡን፣ ሕያው የሆነ ሠላማዊና መሠርታዊ ተቃውሞ ማድርግ አለመቻሉን ነው። ገና ለገና ያደርጋሉ ተብሎ የታሰቡት ተሳደዋል፤ ታፍነዋል አልያም ተገድለዋል። ለመብታቸው የታገሉ ላብ-አደሮች፣ ተበደልን ያሉ አርሶ አደሮች፣ በነፃነት እንደራጅ ያሉ መምህራንና ተማሪዎች፣ በእምነታችን መንግሥት ጣልቃ አይግባብን ያሉ ምእመናን ወዘተ.... ሁሉም በየተራ ተጠቅተዋል። በስደት እንደበግ ታርደዋል። በቁማችው ተቃጥለዋል። ሕዝብ በቃኝ! አሻፈረኝ ቢል እውነቱን ነው።

ከወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ወጣቱ ያተረፈው ነገር ቢኖር እልቂትና ጦርነትን፣ ግፍና ሰቆቃን፣ አፈናና ሽብርን፣ ድህነትና ሥራ አጥነትን፣ ስደትና ውርደትን ነው። የጎሳ ፖለቲካ መሞከሪያ ላቦራቶሪ ያደረገውና ግንጠላን በህግ የደነገገው ወያኔ ወጣቱን ለቀጣይ ጥፋት አመቻችቶታል። ይህን የማያባራ የጥፋት ሂደት እንደጀመረው ሁሉ ሀገሪቱን በማፈራርስ ማሳረግ ይችል ዘንድ የሥልጣን ዘመኑን ለማራዝም ደፋ ቀናውን ተያይዞታል።

የጦር፣ የፖሊስና የፀጥታ ሃይሎችን ለአፈናና ለእመቃ ተግባሩ በመጠቀም ሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሂደት እንዳይኖር ያደረገው ወያኔ በይስሙላ ምርጫ የሥልጣን እድሜውን ሲያራዝም ይህ የአሁኑ ድራማ የመጀመሪያው አይደለም። ወያኔ ጎጠኛና አፍራሽ ዓላማን ይዞ ከአንድነትና ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር ቢወዳደር አየቀሬ ሽንፈቱን እንደሚከናነብ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ወያኔ ከዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሁኔታ መኖር በላይ የሚጠላውና የሚፈራው ነገር የለም። ፀረ-ኢትዮጵያ በመሆኑም በራሱ ተማምኖ ነፃ ውድድር ውስጥ በፍፁም አይገባም። አሳፋሪ


Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011
E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com

የጠባብ ብሔረተኝነት አቋዋሙንና የግንጠላ ታሪኩን ይዞ፣ በሀገርና ወገን ላይ የፈፀመውን ወንጀል ተሸክሞ፣ ከአንድነትና ከዲሞክራሲ ሃይሎች ጋር ጎን ለጎን ቆሞ ራሱን ለምርጫ ማቅረብ ተፈጥሮውም ፈፅሞ አይፈቅድለትም።

ወያኔ ሌላ የአገዛዝ ዘመን በጨመረ ቁጥር ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ወጣቶች ወዴት እንደሚመራቸው አስፍኖት ከቆየው 24 የጨለማ ዓመታት ያየነው ጉዳይ ነው። ወያኔ ለቀጣይ ጥፋት የሚያደረገው ሩጫ ከወዲሁ ካልተገታ ግቡ ኢትዮጵያን ከዓለም የፖለቲካ ካርታ ማጥፋት እንደሆነ ማንኛውም ቅን ኢትዮጵያ የሚስተው አይደለም።

ወጣቱ አብሮና ተባብሮ ሀገር አቀፍ ሃይል ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ለመብትና ለነፃነት የሚደረግ ትግል ሁሌም በአምባገነኖች ተጠቂ መሆኑ የነበረና ያለ ሀቅ ነው። ስለሆነም ይህን አፍራሽና ፀረ- ኢትዮጵያ ቡድን ለማስወገድ በሚደረገው ህዝባዊ ትግል ወጣቱ ብሔር፣ ሃይማኖትና ፆታ ሳይለይ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ እጅ ለእጅ ተያይዞ መጪውን የወያኔ ምርጫ በማከሸፍ ህዝብን የስልጣን ባለቤት ለሚያደርግ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በተባበረ ክንድ መታገል ዛሬም ብሔራዊ ግዳጅ ነው ሲል ኢሕአፓ-ወክንድ አገራዊ ጥሪውን ያቀርባል ።

ወያኔ በፖለቲካ እስረኞች ላይ እያደረሰ ያለውን ፋሽስታዊ ሰየል እናወግዛለን!

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ!

በትግላችን እናቸንፋልን!!

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011
E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com